# አማራና የተዉሰበሰበዉ የኢትዮጵያ ፓለቲካ

ሚኪ አማራ

ይህ ፅሁፍ የተጻፈ ከአንድ አመት በፊት June 15, 2017 ነበር። ዛሬ ላይ ሊከሰት ስለሚችለዉ የፓለቲካ ሁኔታ እንዲህ ተጽፎ ነበር።

በነገራችን ላይ የአንድነቱ ጎራ ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለ ማንኛዉም ሰዉ ንቅል ብሎ ወያኔን እየተዋጋ ያለ ነዉ ሚመስላቸዉ:: ወያኔ እንዲዎድቅ የሚፈልግና ለመጣል ሁሉን ነገር እያደረግ ያለ አማራ ብቻ ነዉ: :ኦሮሞም ቢሆን ያለዉን የፌደራል ስርአቱ ተሻሽሎ የታሪክ ተጎጅነትን በመተቀስ ከሌላዉ ማህበረሰብ በተለየ ከኢኮኖሚዉና የፌዴራል ስርአቱ ተጠቃሚ ሚሆንበትን መንገድ ነዉ እየፈለገ ያለዉ::

ወያኔ ኖረም አልኖረም ፍላጎታቸዉ ይሄ ነዉ:: ኦሮሞዎች በወያኔ ላይ የሚጨክን ልብ የላቸዉም:: የሀገሪቱን ግማሽ ከሌሎች ብሄሮች እየቀማ ሰጥቶዋቸዋል:: በቋንቋቸዉ እንዲማሩ፤ ፍትህና ሊሎች መስል አገልግሎቶች እንዲያገኙ ተደርገዋል:: ስለዚህ ጥያቄያቸዉ የኦሮሞ ልጆች ያዘጋጁት የሀገሪቱ ህገመንግስት አለ (እነ ዶክተር ጊዳዳ፤ ሌንጮ የመሳሰሉት ህገመንግስቱን በበላይነት መርተዉ አዘጋጅተዉታል) ይህ ህገመንግስቱ በትክክል እንዲፈጸምላቸዉ ብቻ ነዉ ሚፈልጉት:: ይሄም ማጅሪቲ በሚለዉ ህግ መሰርት አሁን ባለዉ ስርአት ዉስጥ መንግስት እስከመሆን ነዉ የሚፈልጉት ምንም እንኩዋን አፍ አዉጥተዉ ባይናገሩም:: የነሱ ትልቁ ጥያቄ ህወሃት ተጠቅሟል በቃዉ ተራዉ የኛ ነዉ ነዉ:: ስለዚህ አሁን ባለዉ ስርአት ዉስጥ ኦሮሞ ወይም የኦሮሞ ተዎካይ የሆነ ድርጅት የህወሃትን ያህል ስልጣን ሊኖረዉ ይገባል ነዉ::

ይህ ማለት ደግሞ ዛሬ ህዎሃት ለይቶ ፓሊሲ አዉጥቶ የትግራይን የበላይነትና ተጠቃሚነት በሁሉም መስክ እያረጋገጠ እንዳለዉ ተራዉ ለኦሮሞ ይሁን ነዉ:: እንግዲህ በዚህ አመለካከት ገና እነ ቁጫ፤ ሳሆና፤ የመሳሰሉት ብሄሮች በየተራ ተጠቃሚ እስኪሆኑ ድረስ በነሱ ቤት እኛ አማራዎች እያከክን እንድንኖር ነዉ የተፈለገዉ:: ባለፈዉ አገዉ አማራ ሚባል ሰዉ እንዲህ ነበር የገለጻዉ ኦሮሞወች የስርአቱን መውደቅ የሚፈልጉት በጥንቃቄ እነሱ የበላይ የሚሆኑበት አጋጣሚ የሚፈጠር ከሆነ ብቻ ነው:: ይህ ማለት በየትኛውም አጋጣሚ አማራ ወደ ስልጣን የመጣ የመሰላቸው ቀን ከህወሓት ጋር እጅና ቧንት በመሆን ስርዓቱ እንዲቀጥል ያደርጋሉ::

በኢትዮጵያ ፖለቲካ እየሆነ ያለው ይሄው ነው:: አብዛኛው የኦሮሞ ህዝብና ፖለቲከኛ የፌደራሊዝም ስርዓቱን ይፈልገዋል:: ኦሮሚያ ተብሎ የተሰጠውን ክልል ቢቻል ማስፋት ካልተቻለ ጠብቆ ማቆየት እድሉ ከተገኘ ኢትዮጵያን ወደ ኦሮሚያ መቀየር ወይም የያዙትን ይዞ በመገንጠል አገር መመስረት:: የአዲስ አበባ ጉዳይም ከነዚህ የረዥም ጊዜ እቅድቻቸው አንዱ ነው:: ለአጭር ጊዜ ከአዲስ አበባ ከሌላው በተለየ ሁኔታ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ ሲሆን ለረዥም ጊዜ ደግሞ ትውልዱን ቁቤ በማስተማር ወደ ኦሮሞነት በመቀየር ወደ ግዛታቸው አደላድሎ የመውሰድ ፍላጎት ነው:: ደቡብ አካባቢ ያሉት ብሄሮች ወያኔ እንዲወድቅ አይደለም እንዲያዉም የወያኔ ጠላት ናቸዉ የተባሉትን አማራወችን እየፈለጉ ማሳደድና አይቀጡ ቅጣት መቅጣት ነዉ::

ባለፈዉ ይረጋለም ላይ የታየዉ ይሄዉ ነዉ:: የአንድነት ጎራዉ ወያኔን እያርበደበዱት ነዉ ብሎ እነዲያስብ በሚዲያቸዉ የተነገራቸዉን ብቻ ይዘዉ መሮጣቸዉ ነዉ እንጂ: የሞቱት 32 ሰዎች ሁሉም የአማራ እናቶች፤ልጆችና አቅመደካሞች ነበሩ:: የተቃጠለዉ ንብረት ተሰደዉ ጥረዉ ግረዉ ያፈሩት የአማራዎች ንብረት ነዉ::በባለፉት አራት ወይም አምስት አመታት ዉስጥ ደቡብ ዉስጥ የሆነ ቀዉስ ተፈጠረ ከተባለ አማራ ማሳዉ ሲቃጠል፤ ሲሰደድና፤ ሲገደል የታየበት እንጅ ከወያኔ ጋር ምንም አይነት ቅራኔ አልታየም:: የአንድነት ጎራዉ ይሄን እዉነታ መቀበል ሲያቅተዉ ድርጊቱ እንዲካሄድ ያዘዙት ፌደራል ላይ ያሉት የወያኔ ባለስልጣናት ናቸዉ በማለት ነገሩን ለመሸፋፈን ተሞክሯል::

ይሄ ፈረንጆች Defense mechanism/or self denial ይሉታል:: ባለስልጣናት ስላዘዙ ሳይሆን አጠቃላይ በተለያዩ ብሄረሰቦች ዉስጥ ለአማራ ያለዉ አመለካከት ከትንሽ እስከ ትልቅ እጅግ የተንሸዋረረ ነዉ:: ስለዚህም አማራን ለማፈናቀልና ለመግደል የበላይ ትዛዝ አይጠበቅም brain washed የሆነ ማህበረሰብ ተፈጥሯል ያለማንም ትዛዝ ከታች ያለዉ ማህበረሰብ እርጉዘ እናቶችን ሳይቀር የሚገድል ማህበረሰብ ተፈጥሯል:: ሁሉም እንተወዉና ትናንት የአማራ መሬት የነበረዉ ዛሬ ወያኔ ቤንሻንጉል ብሎ የከለለዉ ዉስጥ ያሉ ሰወች እንኩዋን እንዴት አማራዉ ላይ እየተጫወቱ እንደሚኖሩ እያየን ነዉ:: ቤንሻንጉል

ክልል ዉስጥ በቁጥር አማራ ይበልጣል ነገር ግን ሲፈናቀል፤አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ ሲገደል ያየነዉ አማራዉ ነዉ፡፡ ይሄን ባለስልጣናት አዘዉ ነዉ ብለን ምናልፈዉ ነገር አይደለም፡፡ በየቦታዉ እጅግ አማራ ጠል ማህበረሰብ ህወሃት ማኑዋል እያዘጋጀ ለ 25 አመታት አስተምሮ ፈጥሮልናል፡፡ይሄንም መቀልበስ እማይቻልበት ሁኔታ ላይ ደርሱዋል፡፡

ትግሬዎች በበኩላቸዉ አሁን ያለዉን ስልጣን መልቀቅ ሞትን መጥራት እንደሆነ ይገነዘቡታል፡፡ ህወሃት ስልጣኑን በሰላም ቢለቅ እንኳዋን 26 አመት ከተበደለዉ ህዝብ በተለይም አማራ በትሩን እንደማይችሉት ተግንዝበዋል፡፡ የነሱ አማራጭ እስከቻሉት ልባቸዉ ዉስጥ በሌለች ኢትዮጵያ እያሉ በተቻለ መጠን አማራዉን ለማስደሰት ኢትዮጵያ የሚል ታርጋ የተለጠፈባቸዉ ነገሮች ወደፊት በማምጣት የቤት ስራቸዉን ይሰራሉ፡፡

ካልሆነም እራሳቸዉን ችለዉ አገር የመሆኑን ነገር በደንብ የታሰበበትና በትግራይ ወጣቶች ዘንድ ተቀባይነት ያለዉ ነዉ፡፡ ይሄን ሲያደርጉ ግን ለአማራ ፈንጅ በየቦታዉ ቀብረዉለት ነዉ፡፡ ለምሳሌ ከሱዳን ጋር በደንበር አነካክተዉን ማለፍ ነዉ ሚፈልጉት፡፡

በነገራችን ላይ ሱዳን መሬት ጠይቃ አታቅም ነገር ግን ህወሃቶች አስገድደዉ እንዲጠይቁና በትግሉ ወቅት ላደረጉት እርዳታ መልስ እነዲሆን በደንበር አካባቢ ላሉ ገበሬዎቻችሁ የተዎሰነ መሬት ቢዎስዱ እኛ ደጋፊዎች ነን በሚል አልበሸርን ሳይቀር በአመት አራቴ መቀሌ እየጠሩ አሳምነዉ ነዉ ጥያቄዉ እንዲነሳ የሚያደርጉት፡፡ እንጅማ ትግራይ አፍንጫዋ ስር ያለ የባድመ ደንበር ጥያቄን አንድም ቀን እንኳዋን ሳያወስዋት ምንም አይነት ጦርነትም ሆነ የይገባኛል ጥያቄ ያልተነሳበትን የምእራብ አማራ መሬት በነሱ ሚዲያ በነፋና የደንበር ጉዳይ እያሉ ለባለፉት 10 አመታት ባላላዘኑ ነበር፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ህወሃት የለዉን ስልጣን በመጠቀም ለኢንተርናሽናል ኮሙኒቲዉ ደርግ ማለት ብሄሩ ኣማራ እንደሆነ አድርገዉ በሚገባ አሳምነዋል፡፡ እያንዳንዱ የአሜሪካ ባለስልጣን ከ 90 ወቹ ጀምሮ የነበረ ቀርባችሁ ብትጠይቁት አማራና ደርግን አመሳስሎ ይነግራችሁዋል፡፡ ለዛም ነዉ አሜሪካ ያለ የአንድነት ጎራዉ 26 አመት ጨሁት ጀሮ ዳባ ልበስ የተባለዉ፡፡

ትግሬዎች ብቻ ሳይሆኑ የአሜሪካ የስቴት ዲፓርተመንት የደርግ እርዝራዥች እስከማለት የደረሱት፡፡ በተቃራኒዉ ብሄር ተኮር እንቅስቃሴወችን አሚሪካኖችም ሆነ አዉሮፓዉያኖች የተሸለ ትኩረት ሲሰጡ አይተናል፡፡ ከላይ የጠቀስኩት ጸኃፊ እንዲህ ብሎ ነበር:: ህወሓት መገንጠል ቢፈልግ በእቅዱ ውስጥ ያሉ ሊወስዳቸው የሚፈልጋቸው የአማራ ክልል አከባቢዎችን ለመውሰድ ብቻውን ማሳካት ይከብደዋል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ሰጥቶ መቀበል በሚለው ትርክታቸው የሚሰጡት መሬት የሌላ ቢሆንም ቅሉ አነግ እስከዚህ ያለውን የአማራ ክልል አከባቢ ውስድ እኔ እስከዚህ አከባቢ ያለውን ልጠቅልል ብለው ይስማማሉ፡፡ ዋናው አላማቸው አማራን መውረር እስከሆነ ድረስ ለአፋር ለቤንሻንጉል ለሱዳንም ሊሆን ይችላል የሚሉትን ብለው መሬትህን ሊቀማህ ነው ብለው ሊያዘምቱበት ይሆናል፡፡

ቤንሻንጉል አፋር እና ሌሎቹን ብሔሮች ከተጠቀሙባቸው ቡኃላ ወረው ይይዟቸዋል፡፡ይሄ አይሆንም ማለት ደግሞ የዋህነት ነዉ፡፡ 35 ሚሊየን ኩርዶች እንደዛሬዉ አማራ ምንም አይመጣብንም ብለዉ ሲኖር ከአንደኛዉ የአለም ጦርነት በሁዋላ ኢራቅ፤ሶሪያ፤ቱርክና ኢራን ተከፋፈሉዋቸዉ አሁን መልሰዉ የሚገናኙበት መንገድ አተዉ በራሳቸዉ ግዛት ላይ ሌላ ሃገር ተከፋፍሉቸዉ የኖራሉ፡፡

ዞሮ ዞሮ የአንድነት ሃይሉ በተለይም በዚህ የአንድነት ዉስጥ ያሉ አማራዎች ይሄን አማራዉ የገባበትን እጅግ የተዉሰበሰበ ፖለቲካ አልተረዱትም፡፡ ይልቁንም ጭረሽ ከነኦነግና ህወሃት አሸከሮች ህገመንግስትና ሰትራቴጂ አዉጥተዉ ሌላዉ ማህበረሰብ አማራዉን እንደጭራቅ እንዲያዩት ካደረጉት ከእነ ሌንጮና አረጋዊ በርሄ ጋር ቁጭ ብሎ ሰለኢትዮጵያ መምከር ምን ያህል ፓለቲካዉን እነዳልተረዱት የሚያሳብቅ ነዉ፡፡ ለነገሩ አንድነት ሃይሉ የኢትዮጵያንና የህወሃትን ፓለቲካ ተረድተዉት አያዉቁም ለዛም ነዉ 26 አመት መስመር የሌለዉ አካሄድ የተጓዙት፡፡የገንጣዩ ቡድን እነ ሌንጮና አረጋዊ አሁን ኢትዮጵያ ሲሉ የዉነት የሚመስለዉ ካለ ስህተት ነዉ፡፡ ከነበሩበት ፓለቲካ በግል ችግርም ይሁን በእድሜ ጉዳይ ገለል የተደረጉና አርፎ እቤት መቀመጥ ያልቻሉ እንደገና ተገልብጠዉ ኢትዮጵያ ብለዉ የመጡ ናቸዉ፡፡

በሚቀጥሉት ትቂት አመታትም ለሞት አንድ ኣፋፍ ሲቀራቸዉ ወደዚህ መስመር የሚመጡ የዉሸት ኢትዮጵያኒስቶች ከህወሃት ጎራ እራሱ እንደሚመጡ እንጠብቃለን፡፡ ይህ የሚሆነዉ ግን የራሳቸውን ጥቅም ለማስከበር እስኪያስችላቸው ብቻ ነው፡፡ ከዚያ ይወረውሩታል፡፡ ማሳረጊያዉ ምንድን ነዉ፡ አማራ በአገር ዉስጥ እጅግ ብዙ ጠላት አፍርቱል፡፡ ህወሀቶች ትልቅ ስራ ሰራን ብለዉ ከሚያስቡት ነገር አንዱ አማራን ከሌላዉ ማህበረሰብ የመነጠሉ ስራ ነዉ፡፡

ህወሀቶች የሀገሪቱን የዲፕሎማሲ ስልጣን በመጠቀም አማራን ለአለም ማህበረሰብ ሳይቀር እንደጭራቅ አድርገዉ አቅርበዉናል፡፡ የጥላቻ ስካር ስለያዛቸዉ ነዉ እንጅ በችግራቸዉ ግዜ የደረሰላቸዉ አማራዉ ነበር፡፡ የመለሱልን መልስ ግን ከላይ የተዘረዘረዉ ችግር ነዉ፡፡ ስለዚህም እያንዳንዱ አማራ ቁጭ ብሎ እራሱን መጠየቅ ይኖርበታል፡፡ የሚከተለዉን የትግል ስትራቴጂ ዞር ብሎ ማየት አለበት፡፡